# ነፃ ልውጣ!



ሳላስገዛ ራሴን ለዓላማ
ለዚህ፣ ለዚያ ምክንያት
ብዬ ሳልቆስል፣ ሳልደማ
አማረኝ ሙሉ ነፃነት
ዓላማ ካለው ሕይወት
ነፃ መውጣት!



ለቤት፣ ለልጅ፣ ለሚስት
ለባንዴራ፣ ለሃገር ነፃነት፣
ለዚህ፣ ለዚያ ኃይማኖት
እያሉ ታውሮ ከመዋጋት
ኢ-ዓላማ ሕይወት
ኖሮ መሞት!



የመኖር ዓላማ እክል
በሕይወት፣ በሞት መካከል
ነፃነትን የሚከለክል
በዙሪያ አጥር፣ ክልል
ታስሬ ከምቀጣ
ነፃ ልውጣ!

ገ/ኢ. ጐርፉ።